ፀሐይ ባንክ
TSEHAY BANK

ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎችን ማቅረቢያ እና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ

2018 ዓ.ም.

ማውጫ

ክፍል - አንድ 1

ጠቅላላ 1

1. አጭር ርዕስ 1

2. ትርጉም 1

ክፍል-ሁለት 2

ስለ ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ 2

3. ስለጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ አመሠራረት 2

4.የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ አባልነት መመዘኛ እና የአባላቱ ስብጥር 2

ክፍል-ሦስት 3

በቦርድ አባላት የዕጩዎች ጥቆማና ምርጫ ሂደት የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት 3

5. የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ተግባርና ኃላፊነቶች 3

6. በሥራ ላይ ያለው ቦርድ ተግባርና እና ኃላፊነት 3

7.የቦርድ የዕጩዎች ምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴ ተግባርና እና ኃላፊነት 3

8. የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ተግባር እና ኃላፊነት 4

9. የማህበሩ ፀሐፊ ተግባራትና ኃላፊነቶች 4

ክፍል - አራት 5

ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎች ጥቆማ እና የምርጫ ሂደት 5

10.አጠቃላይ 5

11.የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ 5

12.ህጋዊ ሰውነት ያላቸውን ድርጅቶች በዕጩነት ስለመጠቆም 6

13. የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ምልመላ 6

14. የዕጩዎችን ጥቆማ ስለመቀበል 6

15. ለምርጫ የሚቀርቡ የዕጩዎች ዝርዝር 7

ክፍል-አምስት 7

ድምፅ መስጠት ሥነ-ሥርዓት እና የድምፅ ቆጠራ ሂደት 7

16.የድምጽ መስጫ ወረቀቶች 7

17.ድምፅ የመስጠት ሥርዓት 8
18. የድምጽ ቆጠራ 9
19. የምርጫ ውጤት ስለማሳወቅ እና የውጤት ማስተካከያ ስለማድረግ 9
20. የምርጫ ውጤት ስለማሳወቅ 10
21. የተጠባባቂዎች ዝርዝር 11
22. የምርጫ ሂደት ሠነዶችን ስለማስቀመጥ እና ስለመመዝገብ 11
ክፍል-ሰባት 11
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 11
23. የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት 11
24. የተሻረ መመሪያ 11
25. ይህ መመሪያ በጥብቅ ስለመፈፀሙ 11
26. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ 11

መግቢያ

የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የመልካም አስተዳደር አንዱ መርህ የሆነውን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ግልፅነት በተሞላበት መንገድ እንዲካሄድ ማድረግ ይጠበቅበታል። ታማኝነት፣የአመራር ችሎታና ብቃት ያላቸው ግለሰቦች የቦርድ ኃላፊነት ሲይዙ ለመልካም አስተዳደር መርህ መተግበር ያለው አጋዥነት የላቀ ነው።

በመሆኑም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምርጫ ለማስፈፀም የሚመረጠውን ጊዜያዊ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላት አመራረጥ እንዲሁም የኮሚቴውን ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን እና አጠቃላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ የሚከናወንበትን አካሄድ ለመወሰን እንዲያስችል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው የባንክ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 መሠረት የተዘጋጀው ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ዕጩዎች ማቅረቢያ እና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ በአራተኛው የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ፀድቋል።

ክፍል - አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ***'ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎች ማቅረቢያ እና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ*** 'ተብሎ ይጠራል።

2. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

"ባንክ/ባንኩ" ማለት የፀሐይ ባንክ አክሲዮን ማህበር ነው።

"**ቦርድ**" ማለት በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ወይም ሌላ ስልጣን ባለው አካል የተመረጠ የባንኩ የበላይ አመራር ሲሆን የባንኩን አጠቃላይ አስተዳደር እና የሥራ አፈጻጸም በተመለከተ ስትራቴጂ የመንደፍ፣ የባንኩን ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች መቆጣጠር እንዲሁም የባንኩን ባለአክሲዮኖች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ጥቅም የማስጠበቅ ኃለፊነት ያለበት አካል ነው።

"ዋና ሥራ አስፈፃሚ" ማለት የባንኩን የዕለት ተዕለት ሥራን በዋናነት በበላይነት የሚመራ ሰው ማለት ነው።

"**ዳይሬክተር**" ማለት የባንኩ የቦርድ አባል ነው።

"ገለልተኛ ዳይሬክተር" ማለት ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሰረት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሲሆን ሥራ አስፈፃሚ ያልሆነ፣የባንኩ የአክሲዮን ባለቤት ያልሆነ ፣በባንኩ በማንኛውም የዕለት ከዕለት አስተዳደር ውስጥ የማይሳተፍ፣ ነፃ እና ሚዛናዊ አስተያየት ከሚያዛቡ ማንኛውም ዓይነት ውስጣዊና ውጫዊ የፖለቲካና ከሌሎችም ተፅዕኖዎች ነፃ የሆነ ዳይሬክተር ማለት ነው።

"**ሠራተኛ**" ማለት የባንኩን ሥራ እንዲያከናውን በባንኩ የተሾመ ወይም የተቀጠረ ሠራተኛ ማለት ነው።

"የማህበሩ ፀሀፊ" ማለት የፀሐይ ባንክ አክሲዮን ማህበር ፀሀፊ ማለት ነው ።

"ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ" ማለት አዳዲስ የቦርድ አባላት ዕጩዎች ጥቆማ እና የምርጫ ሂደት የሚቆጣጠር እና የሚመራ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የቦርድ ምርጫ በሚደረግበት ዕለት የሚቋቋም ጊዜያዊ ኮሚቴ ነው።

"የዕጩዎች ምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴ" ማለት ለገለልተኛ ዳይሬክተር አባልነት ዕጩዎችን የሚለይ እና ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሚያቀርብ ኮሚቴ ነው።

"ጠቅላላ ጉባዔ" ማለት የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ነው።

“ተጽዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮን” ማለት ከተፈረመው የባንኩ ጠቅላላ ካፒታል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሁለት በመቶ (2 %) ወይም ከዚያ በላይ ድርሻ ያለው ነው።

“ተጽዕኖ ፈጣሪ ያልሆነ ባለአክሲዮን” ማለት ከተፈረመው የባንኩ ጠቅላላ ካፒታል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሁለት በመቶ (2%) ያነሰ ድርሻ ያለው ነው።

“**ድምጽ**” ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎች በሚቀርቡበትና ምርጫ በሚደረግበት ወቅት ለድምጽ አሰጣጥ ታሳቢ የሚደረገው የተፈረመ አክሲዮን ነው።

ክፍል-ሁለት

ስለ ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ

3. ስለጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ አመሠራረት

3.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚመረጥበት መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ከሚያዘው አጀንዳ የመጀመሪያው ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ ማቋቋምን የሚመለከት ሲሆን በዚህ ጠቅላላ ጉባዔውም ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ይቋቋማል።

3.2. የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው አባላት ቁጥር አምስት(5) ይሆናል።

3.3. ጠቅላላ ጉባዔው ለጊዜያዊ ኮሚቴው አባልነት አስር(10) ዕጩዎችን አቅርቦ በሚያገኙት ድምፅ ቅደም ተከተል መሰረት አምስት(5) አባላት ይመርጣል። የተቀሩትንም በተጠባባቂነት ይይዛል።

3.4. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ አባሎችን በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ መሠረት ይመርጣል።

3.5. የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ውጤት ምርጫው በተከናወነበት ዕለት የሚገለፅ ይሆናል።

4.የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ አባልነት መመዘኛ እና የአባላቱ ስብጥር

4.1 የአስመራጭ ኮሚቴው አባላት፡-

ሀ) የባንኩ ባለአክሲዮን የሆኑ፤

ለ) በኮሚቴ አባልነት ለመስራት ፈቃደኛ የሆኑ፤

ሐ) የባንኩ ተቀጣሪ/ሠራተኛ ያልሆኑ እንዲሁም የቦርድ አባል ያልሆኑ ሊሆን ይገባል።

4.2 ከጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ቢያንስ ሁለቱ ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች መሆን ይኖርባቸዋል።

ክፍል-ሦስት

በቦርድ አባላት የዕጩዎች ጥቆማና ምርጫ ሂደት የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

5. የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ተግባርና ኃላፊነቶች

በሌሎች ህጎች፣በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና በባንኩ መመስረቻ ፅሁፍ ለባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩበታል፡-

5.1. ይህንን መመሪያ የማፅደቅ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማሻሻል፤

5.2. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴን የመምረጥ፤

5.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን የመጠቆም እና የመምረጥ፤

5.4. በቅን ልቦና ብቃትና ታማኝነት ያላቸው እንዲሁም ለመልካም አስተዳደር እና ለባንኩ እሴትን የሚጨምር ሰው በባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት እንዲመረጥ ጥረት የማድረግ፡፡

6. በሥራ ላይ ያለው ቦርድ ተግባርና እና ኃላፊነት

በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች፣በብሔራዊ ባንክ መመሪያ፣በባንኩ የመመስረቻ ፅሁፍ እና በባለአክሲዮኖች በሚወሰኑ ውሳኔዎች ለዳይሬክተሮች ቦርድ የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

6.1. የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ማስመረጥ በተመለከተ በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች ውስጥ በመጀመሪያ አጀንዳነት እንዲካተት ማድረግ፤

6.2. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎችን ማቅረቢያ እና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ በማዘጋጀት እንዲጸድቅ ለጠቅላላ ጉባዔ ማቅረብ፤

6.3. የቦርዱ ዕጩዎች ምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴ ያቀረባቸውን የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ዕጩዎችን ብቁነት በመገምገም እና ተስማሚ እና ትክክለኛ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ዝርዝራቸውን ለጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ማቅረብ፤

6.4. አዲስ የቦርድ አባላት ወደ ሥራ በቀላሉ እንዲገቡ ድጋፍ መስጠት፡፡

7.የቦርድ የዕጩዎች ምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴ ተግባርና እና ኃላፊነት

7.1. ገለልተኛ ዳይሬክተሮችን በተመለከተ የተቀመጡትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ዕጩዎችን መልምሎ ለቦርድ ያቀርባል፡፡

7.2. የዕጩዎች ምልመላ ሂደት፣ የምልመላ መስፈርቶችን፣ የዕጩዎች ግምገማ እና የውሳኔ ሠነዶችን በአግባቡ በመያዝ የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ሹመት ግልጽና ተቀባይነት ያለው ሂደት እንዲሆን ያደርጋል።

7.3. የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ዕጩዎች ብዛት መመረጥ ካለበት የገለልተኛ ቦርድ አባላት ብዛት ቢያንስ ሁለት እጥፍ መሆኑን ያረጋግጣል።

8. የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ተግባር እና ኃላፊነት

8.1. ጠቅላላ ጉባዔ በሚካሔድበት ዕለት የዕጩዎች ጥቆማ እንዲካሄድ ያደርጋል። እንዲሁም የቦርድ አባላት ምርጫን ያስፈፅማል።

8.2. ለምርጫ የሚቀርቡ የዕጩዎችን ዝርዝር ያዘጋጃል።

8.3. ለቦርድ አባልነት የዕጩዎች ጥቆማና የምርጫ ሂደት ግልፅነት፣ ፍትሃዊነትንና ተአማኒነትን መሠረት ያደረገና በሀገሪቱ ሕግ፣ በብሔራዊ ባንክ መመሪያና በባንኩ መመስረቻ ጽሁፍ መሠረት የተካሄደ መሆኑን ያረጋግጣል።

8.4. የምርጫ ውጤት ይፋ ያደርጋል።

9. የማህበሩ ፀሐፊ ተግባራትና ኃላፊነቶች

በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች፣በብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና በባንኩ መመስረቻ ፅሁፍ ለማህበር ፀሐፊ የተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የማህበሩ ፀሐፊ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

9.1. ከመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው አንድ ወር ቀደም ብሎ የማህበሩ ፀሀፊ ለቦርድ አባልነት ጥቆማ እና የምርጫ መስፈርት ዝርዝር ሰፊ ስርጭት ባላቸው የህትመትና የኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎች፣በባንኩ ድህረ ገፅ እና ሌሎች የኤሌክትሮኒክ መንገዶችን በመጠቀም ባለአክሲዮኖች እንዲያውቁት ያደርጋል፡ :

9.2. ማስታወቂያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባላት ማሟላት ያለባቸውን አነስተኛ መስፈርት ማካተት ይኖርበታል።

9.3. የዕጩዎች ዝርዝር መረጃ እና የጠቆሟቸው ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር በአግባቡ መዝግቦ ይይዛል።

9.4. ከጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው የሚሰጠውን የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ውጤት የጠቅላላ ጉባዔው ቃለ-ጉባዔ አካል እንዲሆን ያደርጋል።

9.5. ለዕጩዎች ጥቆማ እና ለምርጫ ሂደት አስፈላጊውን ሠነዶች ያዘጋጃል እንዲሁም ሁሉም የጥቆማና የምርጫ አሠራር መስፈርቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል።

ክፍል-አራት

ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎች ጥቆማ እና የምርጫ ሂደት

10.አጠቃላይ

10.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የዕጩዎች ጥቆማ እና የምርጫ ሂደት በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በጸደቀው በዚህ የአሰራር መመሪያ መሰረት የሚመራ ይሆናል።

10.2. የቦርድ የዕጩዎች የጥቆማ እና የምርጫ ሂደት ለቦርድ አባልነት ብቁ የሆኑ ዕጩዎችን ለመምረጥ የሚያግዝ ነው። ይህ ሂደት በሥራ ላይ ያለውን ቦርድ፣ የቦርድ የዕጩዎች ምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴን፣ በጠቅላላ ጉባዔው ለዳሬክተሮች ምርጫ ዓላማ በየጊዜው የሚቋቋመውን ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴን እንዲሁም ባለአክሲዮኖችን ያካትታል።

10.3. ከጠቅላላ ጉባዔው አንድ ወር ቀደም ብሎ የማህበሩ ፀሀፊ የቦርድ አባልነት ጥቆማ እና የምርጫ መስፈርትን ሰፊ ስርጭት ባላቸው የህትመት እና የኤሌክትኒክ ሚዲያዎች፣በባንኩ ድረ-ገፅ እና ሌሎች መንገዶች ለባለአክሲዮኖች የሚያሳውቅ ይሆናል።

10.4. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ለምርጫ የሚቀርቡት ዕጩዎች ስብጥር በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች አግባብነት ያላቸው ህጎች ያሰፈሯቸውን መስፈርቶች የጠበቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት። በተጨማሪም አስመራጭ ኮሚቴው የዕጩ ጥቆማ ከመካሄዱ አስቀድሞ ለባለአክሲዮኖች ስለ ቦርድ ምርጫ መስፈርቶች ማስገንዘብ ይኖርበታል።

11.የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ

11.1 የዳይሬክተሮች ዕጩዎች ጥቆማ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሚካሄድበት ዕለት የሚከናወን ሲሆን ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ከባለአክሲዮኖች ጥቆማን ይቀበላል።

11.2 ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚወዳደሩትን ዕጩዎች ዝርዝር ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች በማካተት ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል። ዝርዝሩም የሚያካትተው፡-

- የዕጩ ሙሉ ስም እና ዕድሜ ፤
- የትምህርት ደረጃ እና የትምህርት መስክ፤

- የተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ እና ልምድ፤
- ጥቆማውን ያቀረበው የባለአክሲዮን ሙሉ ስም ፤

11.3 ተገቢውን መስፈርት የሚያሟሉ ባለአክሲዮኖች ራሳቸውን በዕጩነት ማቅረብ ይችላሉ።

12. ህጋዊ ሰውነት ያላቸውን ድርጅቶች በዕጩነት ስለመጠቆም

12.1. በዚህ መመሪያ መሠረት በሚካሄድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ምርጫ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል በዕጩነት ከተጠቆመ ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ዕጩውን በቦርድ ውስጥ የሚወክለው ሰው በጥቆማው ሂደት እንዲታወቅ ማድረግና በብሔራዊ ባንክ ለቦርድ አባልነት መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

12.2. በጥቆማ ሂደት ውስጥ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ተወካዩን ካልገለፀ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ያወጣውን መስፈርት የሚያሟላ ተወካይ ምርጫው በተጠናቀቀ በአጭር ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት።

13. የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ምልመላ

13.1. የቦርድ የዕጩዎች ምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ መሰረት ለገለልተኛ ዳይሬክተርነት የመለመላቸውን ዕጩዎች መመረጥ ካለበት የአባላት ብዛት ቢያንስ ሁለት እጥፍ መሆኑን በማረጋገጥ ለቦርዱ ያቀርባል።

13.2. በሥራ ላይ ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ የገለልተኛ ዳይሬክተሮችን ዝርዝር ለጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ ያስረክባል።

14. የዕጩዎችን ጥቆማ ስለመቀበል

14.1የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሚካሄድበት ዕለት ዕጩዎችን በሚከተሉት ሶስት የተለያዩ ምድቦች መሠረት በማድረግ በእያንዳንዱ ምድብ በመለያየት ጥቆማውን ይቀበላል፡-

ሀ) **ምድብ 1፡** ከጠቅላላ የቦርዱ አባላት ብዛት አንድ ሦስተኛ(1/3) አባላት የሚሆኑት ዕጩዎች ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ የሚጠቆሙና የሚመረጡ ይሆናል።

ለ) **ምድብ 2፡** ከጠቅላላ የቦርዱ አባላት ብዛት አንድ ሦስተኛ (1/3) አባላት የሚሆኑ ዕጩዎች በሁሉም ባለአክሲዮኖች ያለልዩነት የሚጠቆሙና የሚመረጡ ይሆናል።

ሐ) **ምድብ 3፡** ከጠቅላላ የቦርዱ አባላት ብዛት አንድ ሦስተኛ (1/3) አባላት የሚሆኑ ዕጩዎች ለገለልተኛ ዳይሬክተሮች የተያዘ ሲሆን፣የዕጩዎች ዝርዝር በሥራ ላይ ባለው ቦርድ የሚቀርብ ሆኖ የሚመረጡት በሁሉም ባለአክሲዮኖች ይሆናል።

14.2. ለምርጫ የሚቀርቡ የቦርድ እጩዎች ብዛት ከእያንዳንዱ ምድብ የሚመረጡትን የቦርድ አባላት ብዛት ሁለት(2) እጥፍ ይሆናል።

14.3. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው የዕጩዎች ጥቆማ መቀበል ከመጀመሩ በፊት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወጡትን የብቁነት እና የተስማሚነት መስፈርቶችን ያሳውቃል፣ ባለአክሲዮኖችም እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟሉ ዕጩዎችን መጠቆም አለባቸው።

14.4. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው በዚህ መመሪያ መሰረት የዕጩዎችን ጥቆማ ከባለአክሲዮኖች ይቀበላል። ዕጩዎቹም በምርጫው ለመወዳደር ዝቅተኛውን የብሔራዊ ባንክ መስፈርት ማሟላታቸውንና ፈቃደኛ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

15. ለምርጫ የሚቀርቡ የዕጩዎች ዝርዝር

15.1. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ለምርጫ መቅረብ ያለባቸው የዕጩዎች ቁጥር በየምድቡ መጠቆሙን ካረጋገጠ በኋላ ጥቆማውን በተቀበለበት ቅደም ተከተል መሠረት የእያንዳንዱን ምድብ የዕጩዎች ዝርዝር ያዘጋጃል።

15.2. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ዕጩዎች እራሳቸውን ለጠቅላላ ጉባዔው እንዲያስተዋውቁ እና በቦርድ አባልነት ለመሥራት ፈቃደኝነታቸውን እዲገልጹ ዕድል ይሰጣቸዋል።

15.3. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው የዕጩዎች ዝርዝር ለጠቅላላ ጉባዔ ተሳታፊዎች በግልፅ እንዲታይ በማድረግ ባለአክሲዮኖች በምርጫ ጊዜ የዕጩዎችን ዝርዝር በግልፅ እንዲያውቁ ያደርጋል።

ክፍል-አምስት

ድምፅ መስጠት ሥነ-ሥርዓት እና የድምፅ ቆጠራ ሂደት

16.የድምጽ መስጫ ወረቀቶች

16.1. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ከሚመለከታቸው የባንኩ አካላት ጋር በመተባበር የድምፅ መስጫ ወረቀቶችንና የምርጫ ሳጥኖችን ያዘጋጃል።

16.2. የድምፅ መስጫ ወረቀቶቹ በእያንዳንዱ የዕጩዎች ምድብ **(ምድብ 1፣ ምድብ 2 እና ምድብ 3)** ተለይተው ይዘጋጃሉ። የምርጫ ወረቀቱም የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) የባለአክሲዮኑን ስም እና ፊርማ፤

ለ) የባለአክሲዮኑን የተፈረመ አክሲዮን ብዛት፤

ሐ) ለጉባዔው ሲባል የተሰጠ መለያ ቁጥር ወይም የባለአክሲዮን መለያ ቁጥር (Shareholder ID) ፤

መ) የባንኩ ስምና አርማ እንዲሁም ማህተም፤

ሠ) ባለአክሲዮኑ የሚመርጣቸውን ዕጩዎች ስም የሚጻፍበት ባዶ ቦታ ወይም መስመር።

16.3. የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ዕደላ በጉባዔው ለመሳተፍ የመጡ ባለአክሲዮኖች ምዝገባና ፊርማ በሚካሄድበት ወቅት ይከናወናል::

16.4. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ከማህበሩ ጸሐፊ እና ከድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ጋር በመተባበር የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በትክክል ለባለአክሲዮኖች እንዲደርሱ እና ድምፅ ከተሰጠባቸው በኋላ በአግባቡ እንዲሰበሰቡ ያደርጋል።

17.ድምፅ የመስጠት ሥርዓት

17.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ እያንዳንዱን ምድብ ለይቶ ለየምርጫ ምድቡ ድምጽ ይሰጥበታል። በእያንዳንዱ ምድብ ያሉ ዕጩዎችን የመምረጥ መብት በአንቀጽ 14 ሥር በተገለጸው መሠረት ይሆናል።

17.2. ባለአክሲዮኖች የሚመርጧቸውን ዕጩዎች ሙሉ ስም በምርጫ ወረቀቶቹ ላይ በመፃፍ እና በመፈረም ወረቀቶቹን በተዘጋጁት ሳጥኖች ውስጥ ይከታሉ።

17.3. በአካል በመገኘት እና በውክልና የሚሰጥ ድምፅ በባንኩ የመመሥረቻ ጽሑፍ መሠረት ይከናወናል። ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን የራሱን አክሲዮኖች ጨምሮ ከተፈረመው የባንኩ ካፒታል ከአስር በመቶ(10%) በላይ ድርሻ ያላቸውን ሊወክል አይችልም። እንዲሁም በሥራ ላይ ያለው ቦርድ አባል፣

ማንኛውም የባንኩ ሠራተኛ፣ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ማንኛውም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ በማንኛውም የባለአክሲዮን ጠቅላላ ጉባዔ ተወካይ እንዲሆኑ አይፈቀድላቸውም።

17.4. ባለአክሲዮኖች የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ሞልተው እንዳጠናቀቁ የባንኩ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ለመሰብሰብ ሳጥኖቹን ያዞራሉ።

17.5. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው በዚህ ሂደት ውስጥ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች የአሰባሰብ ደህንነትና ሥነ-ሥርዓት መጠበቁን እና በየምድቡ ተለይቶ መሰብሰቡን ያረጋግጣል።

18. የድምጽ ቆጠራ

18.1. ድምፅ አሰጣጡ ከተከናወነ በኋላ ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ከማህበሩ ፀሐፊ እና ድጋፍ ሰጪዎች ጋር በመሆን ድምፅ ቆጠራውን ያካሂዳል። የድምጽ ቆጠራው ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀ የኮምፒዩተር ሥርዓት በመጠቀም ይካሄዳል።

18.2. ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው ለእያንዳንዱ ዕጩ የተሰጡትን ድምፆችና ውድቅ የተደረጉ ካርዶችን ይመዘግባል። ውድቅ የተደረገ የድምፅ መስጫ ካርድ ካለ ብዛቱን እና ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት በማስፈር በኮሚቴው ተረጋግጦ ይፈረምበታል።

18.3. የድምፅ መስጫ ወረቀት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ውድቅ ይደረጋል፡-

ሀ) የባለአክሲዮኑን ስም ካልያዘ ወይም የባለአክሲዮኑን የተፈረመ አክሲዮን ብዛት ካላሳየ ወይም የባለአክሲዮኑን የመለያ ቁጥር ካልያዘ ፤

ለ) የባንኩን ስምና ዓርማ ካልያዘ ፤

ሐ) የዕጩ ተወዳዳሪው ስም ካልተፃፈበት ወይም በመራጩ ያልተፈረመ ከሆነ፤

መ) ስርዝ ድልዝ ካለበት፤

ሠ) የተጻፈው ጽሁፍ የማይነበብ ወይም የማይታይ ከሆነ፤

18.4. የድምፅ ቆጠራው ከተጠናቀቀ በኋላ ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው የምርጫውና የቆጠራው ሂደት እንዲሁም የምርጫው ውጤት ትክክል ስለመሆኑ በተያዘው ቃለ-ጉባዔ እና ለዚሁ ሲባል በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ያረጋግጣል።

19. የምርጫ ውጤት ስለማሳወቅ እና የውጤት ማስተካከያ ስለማድረግ

19.1. ከእያንዳንዱ ምድብ (ምድብ 1፣ምድብ 2 ፣ምድብ 3) በተሰጠው ድምፅ ውስጥ ከፍተኛውን የድምጽ ቁጥር ያገኙ እጩዎች እንደተመረጡ ይቆጠራል።

19.2. የተመረጡ ዳይሬክተሮች ዝርዝር ይፋ ከመደረጉ በፊት፣ጊዜያዊ ኮሚቴው በባለአክሲዮኖች ድምጽ በተሰጠው መሠረት የባንኩ ቦርድ ስብጥር የብሔራዊ ባንክ መስፈርቶችን እንዲያሟላ ጥረት ያደርጋል። ቢያንስ ሁለት ሴቶች በዳይሬክተሮች ቦርድ መካተታቸውን ያረጋግጣል።

19.3. ከላይ የተቀመጠውን ስብጥር መጠበቅ ካልተቻለ አስመራጭ ኮሚቴው በተገቢው ምድብ ውስጥ ድምጽ ካገኙ ከቀሩት ዕጩዎች መካከል በመምረጥ አስፈላጊ ማስተካከያዎችን በማድረግ መስፈርቶቹ እንዲሟሉ ያደርጋል።

19.4. በአንድ ምድብ ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዕጩ ዳይሬክተሮች እኩል ድምፅ ካገኙ አስመራጭ ኮሚቴው የትምህርት ደረጃ፣የሥራ ልምድና፤ ጾታን እና ሌሎች የብሔራዊ ባንክ መስፈርቶች መሠረት በማወዳደር ቀሪ ክፍተት ለመሙላት በሚያግዝ ሁኔታ ከዕጩዎቹ በመምረጥ መፍትሄ ይሰጣል። የዕጩዎች ስብጥር የብሔራዊ ባንክ መስፈርት ክፍተት ከሌለበት እኩል ድምፅ ያገኙት ዕጩዎች በዕጣ ይለያሉ። አስመራጭ ኮሚቴውም የእኩል ደምፅ ላይ የሠጠውን ውሳኔ እና ምክንያት በቃለ-ጉባዔ መዝግቦ መያዝ አለበት።

20. የምርጫ ውጤት ስለማሳወቅ

20.1 ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴው የመጨረሻ የምርጫ ውጤት ዝርዝር ለባለአክሲዮኖች ይገልፃል። ዝርዝሩም የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል።

ሀ) ለእያንዳንዱ ምድብ የተመረጡ ዳይሬክተሮች ሙሉ ስምና ያገኙትን ድምጽ ብዛት ፤

ለ) በእያንዳንዱ ምድብ ድምጽ ተሰጥቷቸው ያልተመረጡ ተጠባባቂ ዕጩዎች ሙሉ ስምና ያገኙትን ድምጽ ብዛት ፤

ሐ) የብሔራዊ ባንክ ስብጥር መስፈርት ለማሟላት የተደረገ ማስተካከያ ካለ በግልጽ ከነምክንያቱ ከምርጫ ውጤቱ ጋር መገለፅ ይኖርበታል።

20.2 ከጊዜ ማነስ ወይም በቴክኒክ ምክንያት ወይም በሌላ በማንኛውም አሳማኝ እና ከአቅም በላይ በሆነ አጋጣሚ የድምጽ ቆጠራ ሂደት በጠቅላላ ጉባዔው ቀን ላይ ካልተጠናቀቀ ውጤቱ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በባንኩ ዋና መ/ቤት የማስታወቂያ ቦርድ ላይ እንዲለጠፍና በባንኩ ድረ-ገጽ ላይም እንዲወጣ ይደረጋል።

21. የተጠባባቂዎች ዝርዝር

ድምጽ ተሰጥቷቸው ያልተመረጡ ዕጩዎች ሙሉ ስምና ያገኙት ድምጽ ብዛት በየምድባቸው በተጠባባቂዎች ዝርዝር ተመዝግቦ እንዲያዝ ይደረጋል። ይህም የተጠባባቂዎች ዝርዝር በቦርዱ የሥራ ዘመን ውስጥ ክፍት የቦርድ መደቦች ሲኖሩ ብቁ የሆኑ ዕጩዎች ባገኙት ድምጽ እና የብሔራዊ ባንክ የስብጥር መስፈርቶች መሠረት ክፍት ቦታዎችን ለመሙላት ጥቅም ላይ ይውላል።

22. የምርጫ ሂደት ሠነዶችን ስለማስቀመጥ እና ስለመመዝገብ

22.1. የሁሉም የምርጫ ውጤቶች በእያንዳንዱ ምድብ ያሉ እጩዎች ያገኙት የድምጽ ቁጥር፣ የድምጽ እኩልነት ሲኖር የተወሰነው ውሳኔ ምክንያት፣የብሔራዊ ባንክ ስብጥር መስፈርትን ለማሟላት የተወሰነ ውሳኔ እና የምርጫ ሂደቱ ትክክለኛነትን የሚያረጋግጡ ሠነዶች በአግባቡ መቀመጥ አለባቸው፣ዝርዝር ሁኔታው በባለአክሲዮኖች ጉባዔ ቃለ-ጉባዔ ውስጥ ይመዘገባል።

22.2. የማህበሩ ጸሐፊ የምርጫ ውጤቱና የዳይሬክተሮች ሹመት በብሔራዊ ባንክ እንዲፀድቅ ለብሔራዊ ባንክ ይልካል።

ክፍል-ሰባት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

23. የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሕጎችና መመሪያዎች ይህን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ሥራ ላይ ይውላሉ።

24. የተሻረ መመሪያ

የፀሐይ ባንክ የባለአክሲዮኖች 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጽድቆት የነበረው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎችን ማቅረቢያና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል።

25. ይህ መመሪያ በጥብቅ ስለመፈፀሙ

የጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎችን ማቅረቢያና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያን በጥብቅ በስራ ላይ ያውላል።

26. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በጠቅላላ ጉባዔው ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።